# ከመቃብር ባሻገር ሕይወት.

***<u>የሰው ልጆች ሁሉ ተገዳዳሪ የሆነ የሕይወት ጥያቄ እና አስደናቂ መልስ።</u>***

ውድ አንባቢ ሆይ!! የሰው ሕይወት፣

- መቃብር አይደለም ድንበሩ፣ ቁራጭ ድንጋይ ወይም እፍኝ አመድም አይደለም መታሰቢያው፣
- አንተ ታላቅና አስደናቂ ተስፋ አለህ!
- ያለህ አስደናቂ ተስፋ በምንም አይተመንም፣ በምንም አይመዘንም፣ በምንም አይለካም፣

ስለዚህ እጅግ ደስ ይበልህ።
ይህን ሃሳብ ለመረዳት ይህችን አጭር ጽሁፍ በጽሞና እንድታነብ በፍቅር እጋብዝሃለሁ።

እስቲ ስለራስህና ስለግል ሕይወትህ ለጥቂት ደቂቃዎች አሰላስል።
ምናልባት ሁኔታዎች ፈቅደውልህ በጥሩ ሁኔታ የተማርክና የተሳካልህ፣በአስተዋይ አዕምሮ ታድለህ ዝና የወጣልህ ሥመ ጥር ምሁር ልትሆን ትችላለህ። በሀብትና በዝና የታወቅህ የምድር ኑሮ ሁሉ የቀናልህና ምንም የማትፈልግ የሞላልህ ልትሆን ትችላለህ። ወይም ደግሞ የዚህ ተቃራኒው ያጋጠመህ ሰው፣ ሁኔታዎች ሣይመቻቹልህ ቀርተው ያለምክበት ደረጃ ላይ መድረስ ተስኖህ እንደልተሣካላቸው የሰው ልጆች ሁሉ ጥሩ ዕድል አልገጠምህም ይሆናል። ምናልባትም እንደ ብዙዎች በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ትሆናለህ፣ወይም ጭራሽ ዝቅተኛ የሕይወት ደረጃ ላይ ትሆናለህ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሆኖ ሣለ ወደ የሰው ልጆች ሁሉ አዕምሮ የሚመጣ አንድ ጥያቄ አለ።የትኛውም ዓይነት ሰው ልትሆን፣ በየትኛውም የሕይወት ደረጃና የኑሮ ክልል ውስጥ ልትገኝ ችላለህ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ሁሉ የሚጠይውን ይህን ጥያቄ መጠየቅህ አይቀርም።

- የመጨረሻ ፍጻሜዬ እንዴት ነው ???
- የመጨረሻው አድራሻዬ የት ነው ???
- መጨረሻዬ ምንድነው ???
- ከሞት በኋላ ምን ይሆናል ???

የሚሉትን ጥያቄዎች አንተም ጠይቀህ ይሆናል።ተገቢና የብልህ አዕምሮ ጥያቄ ነው።ታዲያ የዚህ ብርቱና ብዙ ሰዎች ሊጋፈጡት የማይፈልጉት ተገዳዳሪ ጥያቄ መልሱ ምንድነው???
በውኑ በእግዚአብሔር አምሣል የተፈጠረው ክቡር ሰው መጨረሻው መቃብር ነውን ???
በሠለጠነው ዓለም እንደሚደረገው የሰው ልጅ ኖሮ ኖሮ አንድ ቀን ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ተቃጥሎ አንዲት እፍኝ አመድ ወይም አንዲት ከረጢት የመታሰቢያ አመድ ብቻ ሆኖ አበቃ ማለት ነውን???
ሰለዚህም የሰለጠነውም ዓለም ነዋሪዎች መጨረሻቸው**Hospits ከዚያም *****ነው ማለት ነውን ???
ፍጹም አይደለም!!! እናስ!? ይህ ካልሆነ ሌላ ምን ተስፋ አለ ???
የሰው ልጅ ፍጻሜው ሌላ አስገራሚ ነገር እንዳለው የእግዚአብሔር ቃል  ያረጋግጥልናል።

እስቲ አብረን በጽሞና እንከታተል።

የሰው ልጆች ሁሉ የዘለዓለምን ሕይወት እንዲያገኙ አዳኝ ሆኖ የመጣውና ሞትን ያሸነፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠው ተስፋ ቃል ጥቂቱን እንመልከት።

„እውነት እውነት እላችሁዋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ  አይመጣም።“ (ዮሐ. 5፣ 24)
„በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፣ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፍም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣዔ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።“ (ዮሐ.5፤28፤29)
„ከሰጠኝም ሁሉ አንድስ እንኳን እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው የላከኝ አብ ፈቃድ ይህ ነው። ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላዓለም ሕይወትን እንዲያአገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፤እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ።“ ዮሐ 6፣ 39፤40
ሐዋሪያው ቅዱስ ዮሐንስ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን እንዴት እንደወደደና የፍቅሩን መግለጫ አንድያ ልጁን ለሃጢአታንችን ሥርየት እንደሰጠን በወንጌሉና በመልዕክቱ በግልጽ ጽፎልናል።
„በእርሱ የሚምን ሁሉ የዘለአለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲሁ ወዶአልና።በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ሥም ሰላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።“ ዮሐ 3.16፤18
„በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ ፤በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ አለም ልኮታልና፤ፍቅርም እንደዚህ ነው፤እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እርሱን እንደ ወደድነው አይደለም።“ 1ዮሐ 4፤9፤10.
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ  በክብሩ የተገለጠለት ቅዱስ ሐዋሪያው ጳውሎስ የሰው መጨረሻው መቃብር አለመሆኑን በወቅቱ በቆሮንቶስ ከተማ ላሉት አማኞች ስለትንሣኤ በቀላል ምሣሌ ገልጾላቸዋል።
„ነገር ግን፣ ሰው ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዐይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል።አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም፣ የምትዘራው ሰንዴ ቢሆን ከሌላም ዐይነት አንዱ ቢሆን፣ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም፣ እግዚአብሔር ግን እንደ ወደደ አካልን ይሰጠዋል፣ ከዘሮቹም ለእያንዳንዱ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል...የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው።በመበስበስ ይዘራል፤ባለመበሰበስ ይነሣል።በውርደት ይዘራል በክብር ይነሣል።በድካም ይዘራል በኃይል ይነሣል፤ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ... የዚያንም /የአዳምን/ መሬታዊውን መልክ እንደለበሰን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሣለን።“ (1ቆሮ፣ 15፤35-49)
እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ የተገለጠለት ጠቢቡ ንጉሥ ሰለሞን ሥጋ በሰባሽና ወደ አፈር ተመላሽ ቢሆንም ነፍስ ግን ዘለአለማዊ መሆንዋን በትምህርቱ አረጋግጦልናል።
„አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሣይመለስ ነፍስም ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሣትመለስ ፈጣሪህን አስብ።“ (መክ፤12፤7)
„የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንስማ፣ ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና፤እግዚአብሔርን ፍራ፤ትእዛዙንም ጠብቅ።እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፤ወደ ፍርድ ያመጣዋልና።“ ( መክ. 12፣ 13፤14)
<u>ስለዚህ የሰው ልጅ ሁሉ መጨረሻው መቃብር አለመሆኑን በቀላሉ ከዚህ መረዳት ይቻላል።</u>
<u>ከሞት ባሻገር ሕይወት አለ።የሰው ነፍስ ከእግዚአብሔር የተሰጠችው ስለሆነች በመቃብር አትወሰንም።ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት ሁለት ምርጫ አለህ።የምርጫው ውሳኔ በአንተ እጅ ነው።</u> እግዚአብሔር በፍቅር ወደ ዘለአለም ሕይወት ይጠራሃል፤የእግዚአብሔርን የፍቅር ጥሪ ብትቀበል ወደመንግሥቱ እንድትገባ ይቀበለሃል። አንተን ለማዳን የተላከውን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የዘለአለም ሕይወት ታገኛለህ። ኢየሱስም እንዲህ ብሏል፣
„ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።“ (ዮሐ.14፤6)
ሁለተኛው ምርጫ የዘለአለም ፍርድ ነው።ሲኦል ነው። የእግዚአብሔር ዓላማ ግን ከዚህ ከዘለዓለም ፍርድና ኩነኔ ሊያድንህ ነው። እግዚአብሔር ይወደሃል።

<u>አሁን የአንተ ድርሻ፣</u>

- ለአንተ ኃጢአት በመስቀል ላይ የሞተልህን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝህ አምኖ መቀበል ነው።
- ነፍስህን ለታመነው ፈጣሪ አደራ መስጠት ነው።
- ኃጢአትህን በመናዘዝ ፤ንስሐ ግብቶ እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ነው።

<u>የእግዚአብሔር ድርሻ፣</u>

- እንደተሰፋ ቃሉ አንተን በፍቅር ይቀበልሃል።
- የዘለአለምን ሕይወት ይሰጥሃል።

  ምንም አይነት ሰው ብትሆን፣ ምንም አይነት ኃጢአት ብትሠራ በፍቅርና በይቅርታ ይቀበለሃል።
- የመንግስቱ ወራሽ ያደርገሃል።
- በዚህም ምድር ፍጹም የሆነ የአዕምሮ ሠላም፣የልብ ደስታና ዕረፍት ይሰጥሃል።

ይህችን አጭር የእምነት ጸሎት በእውነተኛ ልብ እንድትጸልይ እጋብዝሃለሁ።

*„…እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! አንተ መሐሪና ይቅር ባይ ነህ፣ እኔ ሐጢአተኛና በደለኛ መሆኔን አውቃለሁ ይቅር በለኝ። ስለኔ ሐጢአቴ በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስን የነፍሴ አዳኝና ጌታ አድርጌ ተቀብያለሁ።ከዛሬ ጀምሮ ሰይጣንና አለምን ክጃለሁ፡ሐጢአትንም ትቻለሁ።አንተን አምላኬንና መድሐኒቴን በፍጹም ልቤ ለመከተል ወሰኛለሁ። በፀጋህ እርዳኝ።ስለሰማኸኝና ስለተቀበልከኝ አመሰግንሃለሁ።በክርስቶስ ኢየሱስ አንድያ ልጅህ ሥም ፀሎቴን ስማ አሜን።*

ይህ የአንተ የግልህ ልባዊ ጸሎት ከሆነ እግዚአብሔር መቶ በመቶ እንደ ተቀበለህ በእግዚአብሔር ቃል እውነት አረጋግጥልሃለሁ።

*„ ሁሉን የሚገዛ ጌታ፥ እኔም እቀበላችኋለሁ፣ ለእናንተም አባት እሆናለሁ፣እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ፥ ይላል።“ (2ቆሮ 6፣18)*

*„ አብ ስለወልድ እንዲከበር በሥሜ የሚትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።ማናቸውም ነገር በሥሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።“ (ዮሐ 14፣ 13-14)*

*ማንኛውም መንፈሳዊ ጥያቄም ሆነ የጸሎት ጥያቄ ካለህ ልንረዳህ ምን ጊዜም ዝግጁ ነን። አድራሻህን ከላክልን መንፈሳዊ ጽሁፎችንና ካሴቶችን በነጻ እንልክልሃለን።*

*አድራሻችን፡ Bethlehem Gemeinde*
*C/o CZB Ev.*
*Herwarthstr. 5*
*12107 Berlin*
*Tel. 03076 89045*
*info@bcb.online.org*
*www.bcb.online.org*